# ስለ ቤተሰብ ህይወት ትምህርት ለወላጆች/አሳዳጊዎች ደብዳቤ

ውድ ቤተሰብ/አሳዳጊ:-

ፌርፋክስ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (FCPS) ከመዋዕለ ህፃናት እስከ አስራሁለተኛ ክፍል ድረስ ጥልቅ እና ተከታታይነት ያለው የቤተሰብ ህይወት ትምህርት (FLE) ይሰጣል። የFLE መርሃግብር ተማሪዎች ከሰው ልጅ እድገት እና መሻሻል፣ ግንኙነቶች እና ስሜታዊ እና ማህበራዊ ጤና ጋር በተገናኘ፤ ጤናማ፣ ኃላፊነት የተሞላባቸው፣ ክብር የሚሰጡ እና ህይወትን የሚያሻሽሉ ውሳኔዎችን እንዲሰጡ እውቀትን፣ አመለካከቶችን እና ክህሎቶችን ለመስጠት ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ትምህርት በወላጆች እና አሳዳጊዎች፣ ትምህርት ቤቱ እና ማህበረሰቡ መካከል ለጠንካራ ቤተሰብ እድገት፣ አወንታዊ ግንኙነቶች እና ጤናማ ማህበረሰብ እድገት አስፈላጊ የሆነውን መማር ለመደገፍ እንደ አጋርነት ይታያል።

በክፍል ደረጃ ያተኮረ ዝርዝር የመርሃግብር መግለጫዎች (የትምህርት ዓላማዎች እና ገላጭ አረፍተ ነገሮች) ለእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ በኢንተርኔት ላይ (ኦንላየን) ይገኛሉ። በክፍል ደረጃ ያተኮረ የስርዓተ-ትምህርት ትምህርቶች እና FCPS የማሰራጨት መብት ያለው የተንቀሳቃሽ ምስል/ድምፅ ስራ በኢንተኔት ላይ በSchoology ይገኛሉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች ወደ Schoology ከስቱደንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም (SIS) የወላጅ መለያ ገፅ ተመሳሳይ የመጠቀሚያ ስም እና የይለፍ ቃል በመጠቀም ይገባሉ። በፈጠራ መብት ፈቃዶች ምክንያት፣ ሁሉንም የተንቀሳቃሽ ምስል/ድምፅ ስራ ርዕሶችን ማስተላለፍ አንችልም። ትምህርቶች እና የተንቀሳቃሽ ምስል/ድምፅ ስራዎች እንዲሁ በልጅዎ ትምህርት ቤት ለምልከታ ይገኛሉ፤ በተጨማሪም ትምህርቶች ብቻ በሲቲ ኦፍ ፌርፋክስ ሪጅናል ላይብረሪ ይገኛሉ (ይህ ቦታ ሚዲያ የለውም)።

ወላጆች/አሳዳጊዎች በአጠቃላይ ወይም በከፊል ልጃቸው የቤተሰብ ህይወት የትምህርት መርሃግብር ላይ እንዳይሳተፉ ሊመርጡ ይችላሉ። እንዳይሳተፉ የመረጡ ተማሪዎች አማራጭ የጤና ትምህርት ይሰጣቸዋል፤ እንዲሁም የቤተሰብን ምርጫዎችን ለማክበር የተቻለው ሁሉ ይደረጋል። **በዚህኛው የትምህርት አመት በአጠቃላይ ወይም በከፊል በFLE እንዳይሳተፉ ከፈለጉ፤ እባክዎ ከዚህ ደብዳቤ ጋር የመጣውን ቅፅ ይሙሉ ወይም ቅፁን ከኢንተርኔት ላይ (ኦንላየን) ያግኙት።**
በዝርዝር የቀረበው የክፍል ደረጃ መርሃግብር ዝርዝር እና ተሳትፎ ያለማድረጊያ ቅፆች በFCPS ድረገፅ ይገኛሉ።

- አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- መለስተኛ ሁለተኛ ድረጃ ትምህርት ቤት
- ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

**እባክዎ ተሳትፎ ያለማድረግ ቅፁን ይሙሉ እና ከቤተሰብ ህይወት ትምህርት ክፍለ ጊዜ በፊት ወደ ልጅዎ ትምህርት ቤት ይመልሱት።**

ይኼንን ተሳትፎ ያለማድረጊያ ቅፅ በመጠቀም ልጅዎ እንዳይሳተፉ ካልጠየቁ በስተቀር፤ ልጅዎ በቤተሰብ ህይወት ትምህርት ማስተማሪያ ይካተታሉ። ***ልጅዎ በFLE ማስተማሪያ እንዲሳተፉ ከፈለጉ፤ ይኼንን ቅፅ ለትምህርት ቤቱ መመለስ አያስፈልግዎትም።*** ተሳትፎ ያለማድረጊያ ቅፁን ከመለሱ በኋላ ልጅዎ በFLE ማስተማሪያ እንዲካተቱ ከወሰኑ፤ ለርዕሰ መምህሩ/ሯ በፅሁፍ ማሳወቅ ይኖርብዎታል።

ፌርፋክስ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች በቤተሰብ ህይወት ትምህርት ውስጥ በተካተቱት በጣም ጠቃሚ ርዕሶች እድሜ የሚመጥን ትምህርት ለመስጠት ቁርጠኛ ነው። የFLE ትምህርት የጊዜ ሰሌዳ በተመለከተ መረጃ ለማግኘት እባክዎ የልጅዎን አስተማሪ ወይም ትምህርት ቤት ያግኙ። ለተጨማሪ መረጃ ወይም የFLEን መርሃግብር በተመለከተ ላሉ ጥያቄዎች፣ እባክዎ የትምህርት አገልግሎቶች ክፍልን በ571-423-4550 ያግኙ ወይም በ fle@fcps.edu ኢሚይል ይላኩ።

ከሰላምታ ጋር:-

FCPS የትምህርት አገልግሎቶች ክፍል
ጤና፣ የቤተሰብ ህይወት እና የአካል ማጎልመሻ ትምህርት